# መልስ ለአሲምባ “የኢትዮጵያ ሕዝብ አራዊቶች ፓርቲ” ድረገጽ

## ጌታቸው ረዳ (ኢትዮ ሰማይ አዘጋጅ)

አቶ ሰውየው በሚባል ስም ይድረስ ለአቶ ጌታቸው ረዳ ብለህ ለጻፍክልኝ ኢሕአፓ። መልሴ ይኸው እና። አቶ ሰውየው ማለት ማን መሆኑን እኔም ሆንኩ አንባቢዎቼ በፎቶግራፍም ሆነ በእውነተኛ ስምህ ስለማነውቅህ ለአንባቢ ብትታይ ለማንኛውንም አመች ውይይት ይሆን ነበር። ሆኖም አላደርግም። በዛው እቀጥላለሁ ካልክ ምርጫህን አከብሬ “በአቶ ሰውየው” ልጥራህ እና መልሴን ተቀበለኝ። ርዕሴንም በዛው የገለጽኩት ምክንያት ሰውየው የሚባል ሰውም ሆነ ፎቶ አይተን ስላማናውቅ በሰጠሁት ርዕስ ገብቼበታለሁ” እና መለሴን ተቀበለኝ።



የዋለልኝ ደቀ መዛሙርት አሕአፓ፤አነግ፤ወያኔ እነኚህን ከላይ የሚታዩ አባት ወላጆቻችን አርበኞችንን ነው በአገር ግምባታው ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉትን ነው “ፊውዳሎች፤ ነፍጠኖች፤ መሬት የነጠቁ፤ ነፍጠኞች፤ የፊውዳሉ የአማራ ገዢ መደብ ወታደር፤ የመንግሥቱ የደርግ ወታደር ወዘተ....እያሉ እነኚህ የእምየ የኢትዮጵያ ልጆችን ነው ኢሕአፓ ጀሌዎች ሲዘለፉዋቸው የሚውሉት። ኢሕአፓዎች “ይሰቀል ይሰቀል” እያሉ ያስገደሉላቸውን ንጉሳቸውን በአክብሮት ሲዘክሩ ከላይ የሚታዩትን አገር ዋዳድ አባቶቻችንን ነው ካፍንጫቸው በላይ ርቀው የማይሄዱ በአንዳንድ የኢሕአፓ አባሎች ቤፓልቶኩ ሲዘለፉ የሰማናቸው። ሕሊናቸው የጫጨ አንዳንድ “የኢሕአፓ አራዊቶች” ስለ አማራ መብት የቆሙ እና ስለ አማራ የሚጮሁ በተለይ ሞረሽ ውስጥ ያሉ አማራ ያልሆኑ የወታደር ልጆች ናቸው ሞረሽን የሚደግፉ፤ በማለት ስለ አማራ የሚጮሁ አማራ ያልሆኑትን ዜጎች የወታደር ልጆች በማለት ወታደሮችን ሲያሳንሱ በቴፕ

ድምጻቸው ቀድተናቸው ለታሪክ አስቀምጠነዋል። እነኚህ ምስኪን ላገራቸው የተዋደቁ ዜጎች ናቸው ከሰው በታች እየተደረጉ "ልጆቻቸው "የወታደር ልጆች" እየተባሉ በዝቅተኛ አጠራር እተጠሩ "በማርክስ የመደብ ትንተና ያደጉ" የኢሕአፓ 'ካልቶች' ሲዘለፉ የምንሰማው።

ነብሳቸው ይማረውና በኢንጂነር ሃይዬ ሻውል ንግግር ልጀምር"

**ሃይሉ ሻውል**፡-

"እዛው ያለው አንድ ሰው ከቤቴ አልወጣም ሲል ሚሊሺያ መጥቶ ደብድቦ አጎሳቁሎ ከቤቱ አስወጥቶ ሜዳ ላይ ይጥለዋል። ማን መጥቶ ይከላከልለት? መንግሥት የለ፤ የሌላ ብሔረሰብ መጥቶ አይረዳውም፤ ብቻውን አማራ የሚባለው "በሽታ ይመስል" ሁሉም ....ሌላ ቀርቶ የአገር ውስጥ የፖለቲካ ተቃዋሚዎች እንኳ ሁሉም የአማራ ጉዳይ መስማት አይፈልጉም!" በቃ እውነቱን መናገር ነው፡ አይፈልጉም! በቃ መስማት አይፈልጉም! ከመጀመሪያ ቀን ይህ መንግሥት ከመጣ ቀን ጀምሮ ይህንኑ ነው እየተደረገ ያለው። አላልቅ አለ እኮ ሕዝቡ፤ አላልቅ አላቸው! ማለቅ ከሆነ ሁላችን ይጨርሱን እንለቅ፤ አላልቅ አለ.......!

(ሟቹ ነብሳቸው ይማር ሃይሉ ሻውል)

ኢሕአፓ ኢትዮጵያዊ ብሔረተኛ ነው እየተባለ ስንት ጊዜ ነው የተደሰኮረው? እኔም እራሴ እባካችሁ ተውዋቸው፤እያልኩ ከስንቱ ሰው ጋር ነው በነሱ የተነሳ የተጣላሁት። ዋለልኝን ነካህብን ብለው "እንደ ውርንጭላ ሜዳውን ሁሉ እንጣጥ እንጣጥ እያሉ መንጫጫት ጀመሩ"። በርካታ አባሎቻቸው እየጣሉዋቸው ሄዱ። ዛሬም ሳያፍሩ "እንደ እኛ ያለ ኢትዮጵያዊ ሕብረ ፓርቲ የለም " እያሉ ሲዋሹ ማድመጥ የሚገርም ድፍረት ነው። የወያኔ እና የኢሕአፓ ካልቶች ልክ የሃይማኖት ካልቶች ስሕተታቸው ማየት የማይፈልጉ "ዲፌክትድ" የሆኑ 'ሲከረከሙ የተበላሹ ድንጋዮች' ናቸው። እኔን መንካት እሳት ጋር መጫወት ነው የናንተን ማንነት ይበልጥ ያበላሻል ስል "አለን፤አለን" አላችሁ። ሁለት ውርጋጦች እኔ ጋር በኢመይል ሊምቦጫረቁ ሞከሩ። መልስ አልሰጠኋቸውም። አንዱ እማ ሁሌም የሚገርመኝ ከረር ያለ የግራ ጥፊ ቀምሶ አያውቅም መሰለኝ ከአቅሙ በላይ የሚዘል ነው። ፓል-ቶክ ውስጥ ተዘፍቆ ኢሕአፓ

ተቾ፤ዋለልኝ ነካ እያለ ሁሌም የእኔን ስም የሚያነሳ ስለ ኢሕአፓ አርበኝነት ሲያወራ ከጉልበቱ ይልቅ ምላሱ የረዘመ "ኮስማና" በኢመይል መነፋንፍ ሞከረኝ እና ንቄ ተውኩት። አሁን አሁን ሳስበው <u>የሕሊና ቀውስ ያለውም ይመስለኛል</u>። ትግሬዎች አንድ የምንለው ነገር አለ። <u>እዛ ዳዋ እተምጸኦ አለዋ"</u> ይላሉ። ስለዚህ "ካራቲስቶችና ጉልበተኞች" እባካችሁ እንደ ዳዋዋ ሰውን ባትነካኩ ይመረጣል። ኣደብ! ይላል ትግሬ ኣደብ! (ጸባይ!)።

በኢመይል የሚነፋነፉ ስለ የኢሕአፓ *ካራቲስቶች* እዚህ ላቁምና ወደ አሲኢምባ ድረገጽ አዘጋጆቹ ወደ ክቡራን ኢሕአፓዎቹ ልመልሳችሁ። አንድ ወዳጄ፤ እባክህን መልስ አትስጣቸው፡ ባንተ ጽሑፍ ምክንያት "ኢሕአፓ ዛሬም አለ" ለመባል እንዲረዳቸው ያደረጉት ርካሽነት ነው እና "ዝጋቸው" ብሎኝ ነበር። እኔም ከካልቶች ጋር መነጋገር ጊዜ ማባካን ነው ብየ ልዘጋቸው አስቤ ነበር። ሆኖም "እባክህ" "አሉ" እንድንባል መልስ ጻፍልን የሚል በድረገጾች ልከው አስለጠፉ። እኔም ልመና መስሎ ስለታየኝ መልስ ልጽፍላቸው ወሰንኩኝ። በኔ ጽሑፍ ኢሕአፓን በህይወት መኖር የሚያስተዋውቅ ከሆነላችሁ ደስ ይበላችሁ እነሆ። ይህ ጽሑፍ "ታገሱ" የሚል መግቢያ ነው። እንደ አማላችሁ እንደ "የጋንግ ጸባያችሁ" እዛው ድረገጻችሁ እንደ ጉንዳን የካልት ጩኸት እየተንጋጋችሁ እንንጫጫለን ብላችሁ እንፍጨረጨራለን ካላችሁ ሌላ ትልቅ ሸክም ይዞ ይመጣል። ምርጫው የናንተው ነው። ስለዚህ በዚህ ቢበቃችሁ ብትታገሱ ጥሩ ነው።

በወያኔ መርዝ ተገደለ የሚባለው ዘፋኙ ኪሮስ አለማዮህ "<u>ኣለኹ እየ ዝብልየ"</u> የሚል ዘፈን ነበረው። <u>"አለሁኝ ነኝ የምለው"፤</u> ይላል። እነኚህ የኢሕፓ ሚሰኪኖች <u>"አለን"</u> ይላሉ። <u>አለን የማይል ማን አለ?</u> የአበሻ የአነጋገር ባህላችን እኮ ነው። አልጋ ላይ ታምሞ ተኝቶ "በጣረሞት ተይዞ" አንድ እግሩ ጉድጓድ ገብቶ "እንደምን አለህ?" ስትለው <u>"ይኸው አለን መቾም"</u> ነው የሚለው የአበሻ ባህል ነው እና "አለነው" ይላል። አይደለም እንዴ? እነኚህ ወንድሞች ደግሞ "ኢሕአፓ የሞተ እንዳይመስልህ ኢሕአፓ አለ" ብለውኛል። መኖር እማ ስለኖራችሁ እኮ ነው "አለን" የሚል ጽሑፍ እየጻፋችሁ ያላችሁት። ነገሩ ኢሕአፓ ሊኖር ይችላል፡ ስለኖራችሁ እማ ወደ ውጭ አገር መጥታችሁ እየኖራችሁ ነው አይደለም

እንዴ? የመኖር ዕድሉን ያላገኙት በናንተው ጓዶች በፓርቲያችሁ ነብሰ ገዳዮች ጥይት ያልኖሩት በናንተው በኢሕአፓ ነብሰገዳዮች የተገደሉ ምስኪን ኢትዮጵያዊያን ግን እዚህ እንደ እናንተው ተሰድዶ የመኖር ዕድል ሳያገኙ ባጭር ቀጫችሓቸው። እነሱ ግን የሉም አይደለም እንዴ? አዎ መኖሩን እማ እየኖራችሁ ነው። ዕድሜ ለአሜሪካኖች በሉ።

እነ ጸጋዬ ደብተራው'ማ ሰው አስጨርሰን የት ነው የምንፈረጥጠው ብለው ካገራችን መሬት እንቀበራለን እንጂ "አንወጣም" ብለው በወየኔ ጥይት ሲቆሉ "የአለን ግሩፖች" ብልጦቹ ፈርጥጣችሁ ጥላችኋቸው ወደ እምየ "ኢምፔሪያሊዝም ይውደም" ስትሉዋቸው ወደ ነበረው አሜሪካና አውሮጳ ተጠልላችሁ "አለን" ትላልችሁ። አዎን አላችሁ፤ መኖርያዎችም አላችሁ።በሽሽት እማ እንኳን አሜሪካ ውስጥ ከኢሕአፓው አባል ከፈረንጁ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር ዶ/ር ዊሊያም ሄስቲንግስ ሞርተን መኖርያ ቤትም መጠለያ እና መሸሸጊ````ያም አድርጋችኋል። ሁሌም እንደሸሻችሁ እና እንደኖራችሁ አላችሁት፤ዛሬም አዎን "አላችሁ"።

ኢሕአፓ ወደ ፍርድ አልቀረበም እና ለወደፊቱ ለፍርድ መቅረብ ካለባቸው አንዱ ኢሕአፓ እና ወያኔዎች ናቸው ስል ለምን እንደምትንጫጩ አልገባኝም። እራሰችህ መከራ መጥራት ነው። ብዙ ሰው የገደሉ አሜሪካ እና ኢሕአፓ እንዲሁም ካናዳ ተጠልለው ልክ እንደ ደርግ ገራፊዎች የትም ተበትነው እንደሚኖሩ እናንተ የምታውቁት ሃቅ ነው። ይህ ሁሉ ነብሰገዳይ የት ገባ ብላችሁ ልትነግሩን ነው? አዲስ አበባ ቀረ? አሲምባ ቀረ? ወይስ ኢሕአፓ የሚባል ገዳይ አሰማርቶ ሰው ሲገድል አልነበርም ልትሉን ነው? ኢሕአፓ እራሳችንን ለመከላከል ("ቡልሽት! መከላከል") ስንገድል ነበር ብላችሁ የምትሰነዝሩት ምክንያታዊ መልሳችሁ "ራሳችንን ላለመገደል ገዳዮች አሰማርተን ነበር" የምትልዋቸው "ገዳዮች የምትልዋቸው፤ነብሰ ገዳዮችስ" የት ገቡ? እዚህ እናንተው ጋር የሉም? መልስ ስጡን እንጂ። እራሳችን ለመከላከል ሰው እናስገድል ነበር ይላል ፓርቲያችሁ "ገዳዮቹ" ለምን አትነግሩንም ለምን ሰው ሲገድሉ ነበር? ወደዳችሁም ጠላችሁም፤ ኢሕአፓ "ኢትዮጵያዊ ሕብረ ፓርቲ" ምናምን "ቡልሺት!" መመጻደቁን እርሱት እና "ለፍርድ ትቀርባላችሁ!"። ገራፊየ ይኼ ነው እያላችሁ የደርግ

ገራፊዎች የምታስይዙ ያህል በቅርቡ ቤተሰቦቻችን ሲገድል የነበረ የኢሕአፓ አባልም ይህ ነው ለፍርድ ይቅረብ ብለው እንደሚመጡ ምንም አልጠራጠርም። አፉችሁ ብትዘጉ ጥሩ ነው። “ታይም ፎር ዩ ቱ ሻት ኣፕ!!!!!”

ስለ ጠቀሳችሁት ስለ ጸጋየ ደብተራው አንስቼ በሰብኣዊነት ተነሳስቼ ወያኔዎችን የት አደረጋችሁት ማለቴ የሚያስመሰግነኝ እንጂ ለናንተ የፖለቲካ ርካሽ መጠቀሚያ እንድትገለገሉበት ብየ አልነበረም። አሁንም አሱም ሆኑ ጓዶቹ በህይወት እንዲኖሩ ምኞቴ ነው። የነሱ በህይወት መኖር ስለናንተ ፈርጣጮች የሚነግሩን ብዙ ነገር ይኖራቸውና ይነግሩር ነበር ብየ እገምታለሁ። የተጸጸቱባቸው ወንጀሎችም ከነበሩ ግልጽ አድርገው ይቅርታ ይጠይቁ ነበር ብየ እገምታለሁ። ከሸሹት ጋር አልሸሹም እና ስላልታደሉ እንደ እናንተው “የመኖር ዕድል ባያገኙም” እንደ <u>የቁም ሙታኖች</u> አለን ባይሉም ፤በታሪክ ግን በመጥፎም በደግም ይታወሳሉ። ታሪክ ለባለ ታሪኩ!

ይኸ ድረገጽ ከኢሕአፓ ፓርቲ ጋር ግንኙነት የለውም “እኛ ከኢሕአፓ ግንኙነት የለንም፤ግን ኢሕአፓ ደማችን አጥንታችን ነው “ ስለምትሉት ቅዠት” ለምን እንደሚያቃዣችሁ ሊገባኝ አልቻለም። ዓይጋም ድረገጽም እኮ ከወያኔ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም ነው የሚለው። አሲምባ ድረገጽ የሚሸተው “ኢሕአፓ፤ኢሕአፓ” ነው የሚሸተው። አጥንቱም ደሙም ኢሕአፓ ነው። ‘ዓይጋ-ፎረምም’ ሆነ ‘ትግራይ ኦን ላይንም’ የሚሸተው ‘ወያኔ’ ነው። አሲምባ “ኦርጋናይዘሽን ነው”፤ <u>“የሸሹ. ዳት ኦርግ”</u> ብላችሁ ብትሉት ሌላ ነገር ነው፤ ግን “አሲምባ. ኦርግ” (ኢሕአፓ ማለት ሲሆን) “ደደቢት. ኦርግ” ብሎ ሲል “ወያኔ” ማለት ነው። ደደቢት.ኦርግ ብሎ አንድ ድረገጽ ቢወጣ በቀጥታ የሚነግረን “ወያኔ መሆኑን ነው። በአሲምባ የሚተላለፉት ዜናዎች፤ ትችቶች፤ ጽሑፎች ሁሉ “ኢሕአፓ” ነው። <u>አሲምባ.ኦርግ</u> ሲል ደግሞ <u>“ኢሕአፓ”</u> ማለት ነው። ስለዚህ ከኢሕአፓ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም ብትሉም ባትሉም፤ እኛ ታዛቢዎች የምናየው እና ኢሕአፓ የነበሩ ከተገነጡሉ መካካል የነገሩኝ ግን ኢሕአፓ ብዙ ድረገጾች በተለያየ ስም ከፍቶ ፕሮፓጋንዳው እንደሚያስተላልፍ ተነግሮኛል። ሌላ ቀርቶ ኢሕአፓችሁ ለሁለት ሲከፈል የኢሳያስን ወገን ደግፋችሁ ሌሎቹን

ስትጨፈጭፉ የነበረውን ዘገባችሁ እዛው አሲምባችሁ ላይ አልነበረም? ሌሎቹ የፕሬስ ምናምን መስጪያ ነው። ሌላው ደብተራ ይላል፤ሌላው ስንቱን እንቁጠር? ደብተራው ድረገጽም "ኢሕአፓ" አይደለም ስትሉን እሺ ይሁንላችሁ። አሲምባችሁ ደግሞ ሌሎቹን የምላሳችሁ መግረፊያ፤ ማስፈራሪያ፤ ራዲዮ ማሰራጪያ ነው። ኢሕአፓ ድረግጽ ማለት ከዚህ ወዲያያ ምን የሚሉት ኢሕአፓ ድረገጽ ሊፈይድ ይችላል?

"ከአማራ በላይ አማራ ለመሆን" ብላችሁ ለከፋችሁኛል። ኢሕአፓ ያንኳሰሰው እና ለውርደት የዳረገው "አማራ ማሕበረሰብ" ቆሜ ስለ አማራ መቆሜ "ትግሬ ትግሬ ነው" ከሚሉት ዘረኞችና ግብዞች የሚለያችሁ ነገር የለም። አማራ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ነው። ስለ አማራ መቆሜ የዜግነት መብቴ ነው።አማራ ያልሆነ ስለ አማራ አያገባውም ብሎ የነገራችሁ የትኛው የአሲምባ ፈላስፋ ነው? አማራ መሆን ስለ አማራ ማሕበረሰብ ችግር ይቆማል ብሎ የነገራችሁስ ማን የሚሉት ሞኝ መምህራችሁ ነው? ብትነገሩኝ ጥሩ ነበር። ዋለልኝ እና እንድርያስ እሸቴ እኮ ከፍተኛ ምሁራን እና አማራዎች ናቸው። ታዲያ እንቆቅልሹ ባልገባን ሁኔታ ከአብራኩ ወጥተው አማራን እንደሌለ አፈር ድሜ ነው ያበሉት።አይደለም እንዴ? አማራው የወያኔው አሽከር አለምነህ መኮንንስ አማራውን ምን ብሎ ነበር ሲዘልፈው የነበረው? ተስታውሳላችሁ፤ አይደለም እንዴ? አማራ መሆን ለአማራ ካልቆመ አማራነቱ ምን ይፈይደዋል። እንዳውም አማራ ከሆናችሁ ተቀዳሚ ተጠያቂ የማደርገው ከአብራኩ የወጡ ወላጆቹ ሲዋረዱ እንደእናንተው ያለው "ከንቱ ማፈሪያዎች" ወላጆቻቸው በዘረኞች ሲደበደቡ፤ በሰው አራዊቶች ሲበሉ "አልተበሉም እያላችሁ" ለበሊታዎቹ ጥብቅና ቆማችሁ ስለ አማራ የቆመን አፉን ለመስዘጋት የምትሞክሩ እናንተን የመሳሰሉ "የተረገሙ ሽንቶችን" ነው ተጠያቂ የማደርገው። ታዲያ አማራዎቹ ወላጆቻቸው እና ወንደም እህቶቻቸው ሲሰደቡና ሲገደሉ ዝም ብሎ የተመለከተ አማራ እና አማራ ነኝ ብሎ ተሳዳቢውን ዋለልኝ መኮነነን "አርበኛ "የሚያደርግ ኢሕአፓ እና አንደ እናንተው ያለው አማራን የሰደበ ዋለልኝን በምርጥ ኢትዮጵያዊነት ሰይሞ "በስሙ ድረገጽ ያቋቋመ" አማራዎችም ሆናችሁ ኦሮሞ ወይንም ትግሬ (የፈለጋችሁት ሁኑ) በምን መለኪያ ነው እኔን "አማራን የመከላከል መብት የለህም ስትሉ

ከአማራ በላይ አማራ ለመሆን የቃጣው ብላችሁ እኔን መብት የለህም የምትሉኝ? እናንተ ማን ትባላለችሁ? በምን ሞራላችሁ ነው ስለ ኢትዮጵያ እና አማራስ ጥብቅና ቆማችሁ ትግሬ ስለ አማራ አያገባውም የምትሉት እባካችሁ? ዛሬም ከስህተታችሁ መማር አልቻላችሁም? በየቀኑ ወደ ባሰ አዘቅት እየገባችሁ እኮ ነው።

አማራ በቤንሻንጉል ከነ ነብሱ የሰው አውሬዎች ቀቅለው ሲበሉት እናንተ አማራዎችን ምን ነበር ያላችሁት? የተበሉ ሰዎች እንዳሉ ከሸሹት ሰዎች በራዲዮን ቃለ መጠይቅ ሲደረግላቸው እናንተ "አረመኔዎችና ካሃዲዎች" (ጸረ አማራዎች እና ዋለልኝ መኮንኖች) ምን ብላቸችሁ ነው ከመበላት የሸሹ አማራ ገበሬዎች እያናናቃችሁ መልስ የሰጣችሁዋቸው? ኢትዮጵያ ብንገባ (አሁንም ሳንገባ፡ ዛሬም ስለ እናንተ ኢሕአፓዎች ሕዝቡ ተነግሮታል) ለሕዝብ ይህንን ብነግርላችሁ ኢሕአፓ በምድረ አማራ ጭራሽ እንዳይገባ ማድረግ የሚያስችል አሳፋሪ "ክሕደት" አደለም የፈጸማችሁት? የሞተውን ኢሕአፓ የምታሰድቡ እናንተ ናችሁ። አሲምባ ያላችሁ ካልቶች አፋችሁ ብትይዙ ኖሮ ኢሕአፓ እንዲህ ያለ ተደራራቢ ብትር አይደርሰውም ነበር። ከጥቅሙ ይልቅ ለኢሕአፓችሁ ጉዳት እንዲደርስ እያደረጋችሁ ነው። እነዚህ ከናንተው የተለዩ ሰዎች በዚህ ዓይነት ንትርክ ገብተው አያውቁም፤ መናገር የለባቸው ነጥብ ካለም በስርዓት ተናገርው ዝም ይላሉ። ስለ ሻለቃ ፍስሃ ደስታ መጽሐፍ ስትንጫጩ፤ ከናንተው የተለዩት ኢሕአፓዎች በራዲዮን ቀርበው የመሰላቸውን እርማት እና "ምስጋና' አቅርበው በጨዋ መልክ ነው ያቀረቡት። እናንተ ግን ሰዎችን ማስፈራራት በኢመይል መስደብ፤መጮህ ስም ማጥፋት መዘባረቅ፤ነው ስራችሁ። ከወያኔ እና ከጽንፈኛው ውሃቢስቶቹ ቀጥሎ ያለው አደገኛ ካልት (መማር የማይችል ካልት) እናንተ ናችሁ።

"አማራዎች የቤንሻንጉል ሕዝባችን ለመስደብ ሲሉ ሰው ይበላል፤ሃይማኖት የላቸውም ለማለት ነው ይህ የውሸት ወሬ እየነገሩን ያሉ" ብላችሁ አደለም የጻፋችሁባቸው? ያውም እኮ መግለጫው እና ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው ከአደጋው የሸሹ ሰዎች ሲናገሩ "ሃይማኖትት የላቸውም"

አላሉም። "ሃይማኖታቸው ብዙዎቹ እስላሞች ናቸው" ነው ያሉት። ሃይማኖት የላቸውም ፤ ጉሙዞች አረመኔዎች ለማለት ተፈልጎ ነው አማራች ተበሉ እያሉ አማራዎቹ እያወሩ ያሉት" እያላችሁ ያልተነገረ ነገር ስትዘባርቁ ነበር። ሃይማኖት ያለው ሰውን በልቶ፤የሰው አንገት፤ የእርጉዞች ሆድ በቢላዋ መኸርኀ፤ አንገት ቆርጦ አያውቅም ብሎ የነገራችሁ ማን ነው? ውቃቢ የራቃችሁ የኢሕአፓ ካልቶች "አማራን እንደጠላት" የመቁጠር እንደ ጡት እናታችሁ የዋለለኝን ጸረ አማራነት ጡት ሕሊናችሁ እየጠባ ስላደገ፤ዛሬም ስለ አማራ የቆመ ሁሉ 'ትግሬ ትግሬ ነው፤ ከአማራ በላይ አማራ ለመሆን መሞከር" እያላችሁ የአማራ ጠላትነታችሁ ለማጉላት ስትሉ፤ "ከኤርትራኖች በላይ ኤርትራዊ መሆን" እንደምንለው ሁሉ አማራ እንደካሃዲ ቆጥራችሁት ሌለው ኢትዮጵያዊ ዜጋ ፡እኔም አማራ ነኝ" አትበል 'አማራ' ብቻውን ቢበላ፤ቢታረድ እኛ ኢሕአፓዎች ብቻ ነን የምንናገርለት ስትሉ ትንሽ አታፍሩም? ይህ የበከተ የተበላሸ "ኮራፕት" የሻገተ "ቆሮቆንዳም ብስለታችሁ" ጸረ አማራ ፖለቲካችሁ ከመኻታችሁ ስትነሱም ስትተኙም እንደ በሽተኛ ሰው ያቃዣችኋል።

ደግሞ "ከዓይነ ሕሊናችን ተደብቆ የነበረው የኢሕአፓ ጉድ አቻምየለህ ታምሩ (እውነትም አቻምየለህ) ስለነገረን "አቻምየለህ ወያኔ ነው" ትላለችሁ። ትንሽ አታፍሩም? በቃ ያጋለጣችሁ ሁሉ "ወያኔ ነው" ስለ አማራ የቆመ ትግሬ ሁሉ "ከአማራ በላይ አማራ መሆን ነው"። ስንት ጊዜ ነው ለመሪያችሁ እያሱንም ሆነ ለናንት ስለ ወጣው ሰነድ መልስ ስጡበት እና መስመራችሁ እንወቀው ብየ የወተወትኳችሁ? መልስ ከመስጠት ይልቅ "አቻምየለህ ወያኔ ነው" 'ጌታቸው ከአማራ በላይ ለአማራ ጥብቅና እቆማለሁ ይላል" ብሎ ከመቦትለክ ባሻገር አቻምየለህ ወያኔ መሆኑን ልታረጋግጡ አልቻላችሁም። ካሁን በፊት የናንተን ጸረ አማራነት እና ጸረ ኢትዮጵያ መሆናችሁ ሳላውቅ "ስደግፋችሁ እና ስከላከልላችሁ" ነበር። አሁን ግን እግዚሃር ይስጠው አቻምየለህ መጥቶ "ኢሕአፓ" ማለት ይኼን ይመስላል ሲለን "ክው!" ነው ያልኩት። ትንሽ ሳትቆዩ አቻምየለህ የነገረንን በበግ ለምድ የለበሳችሁት የተኩላ ቆዳ ተጋለጥ ሲላችሁ የቤንሻንጉል አማራዎች በሰው መበላታቸውን ጭራሽ ሰዎቹን ስትሰድቡ ሳነብብ "ለክውታ-የ፤ ተጨማሪ ክውታ ሰጠኝ" እና ምን እሚልዋቸው አራዊቶች

ናቸው አልኩኝ። አውነትም "የኢትዮጵያ ሕዝብ አራዊቶች ፓርቲ"። ኡፍ! እባካችሁ እንተኛበት!

ነብሳቸው ይማር እና አቶ ሃይሉ ሻውል ለናንተ ጻረ አማራ እና መሳሰሉ ርካሽ ተቃዋሚዎች የሚሉት ነገር ነበራቸው፤ ከኢሳቱ መሳይ መኮንን ጋር ቃለ መጠይቅ ሲያደርጉ እንዲህ ብለው ነበር፤

"

**ሃይሉ ሻውል፡-**

የተጠናከረው ጠንካራ ረዚስታንስ ቆሞ እምቢ የሚል ስለጠፋ ነው። አንድ ሰው ከቤቴ አልወጣም ሲል ሚሊሺያ መጥቶ ደብድቦ አጎሳቁሎ፤ አቁስሎ፤ ከቤቱ አስወጥቶ ሜዳ ላይ ይጥለዋል። ማን መጥቶ ይከላከልለት? መንግሥት የለ፤ የሌላ ብሔረሰብ መጥቶ አይረዳውም፤ ብቻውን አማራ የሚባለው "በሽታ ይመስል" ሁሉም ....ሌላ ቀርቶ የአገር ውስጥ የፖለቲካ ተቃዋሚዎች እንኳ ሁሉም የአማራ ጉዳይ መስማት አይፈልጉም!" በቃ እውነቱን **መናገር** ነው፡ አይፈልጉም! በቃ መስማት አይፈልጉም! ከመጀመሪያ ቀን ይህ መንግሥት ከመጣ ቀን ጀምሮ ይህንኑ ነው እየተደረገ ያለው። ለወር ትጮሃለህ፤ ነገሩ ተድበስብሶ እንደገና ተረስቶ ዝም ይባላል፤ ከወር በኋላ ሲከሰት እንደገና ተድበስብሶ ይታለፋል፤ እንደዛ እያለ ኮንሲስታንት/ቀጣይ/ የሆነ፤ በሕብረት የሚሰራ በውጭም በውስጥም የለም።"

ይህንን አይገባችሁም? "የፖለቲካ ተቃዋሚዎች እንኳ ሁሉም የአማራ ጉዳይ መስማት አይፈልጉም!" በቃ እውነቱን **መናገር** ነው፡ አይፈልጉም! በቃ መስማት አይፈልጉም!" ይህንን ሰምተን ስለ አማራ የቆምን ዜጎች "ከአማራ በላይ አማራ ለመሆን" ብላችሁ ስትሰድቡኝ ምን እምትባሉ አራዊቶች ናችሁ? "መስማት አልፈለጋችሁም" የአማራን ብሶት ሰምተው የጮኹትን አትዝለፉን በቃ! ። የተጠቁ ከአደጋው ሸሽተው የመጡ ገበሬዎችን "ዋሾች" አትበልዋቸው። እውነትም ኢሕአፓን ይበልጥ ችግር ውስጥ እንዲገባ የባሰውኑ እንዲሰደብ የምታደርጉት እናንተ ናችሁ። ከኔ ጋር ስትላከፉ ብዙ ችግር ታመጡለታላችሁ። እረፉ! አደብ!

ድረገጽ መስርታችሁ ስለ ዋለልኝ የምትቦተልኩት የሻገተው "ዴድ - ብረይን" "ቆሮቆንዳው ብስለታችሁ" እንዲነቃ ሁለት ነገር ላስምርና ልጨርስ፡ አረ ወደ እዚያ! ኡፍ!

አለን እንድንባል እባክህ መልስ ስጠን ብላችሁ ስለለመናችሁኝ እንጂ እውነት ጊዜ ማባከን ነው። ደግሞ ከማይለከፍ ሰው ጋር ነው እየተላከፋችሁ ያላችሁት። እስካሁን ድረስ እኔን ያለማወቃችሁ አሁንም ይገርመኛል። እንደ እንናትው ያሉ ቆሮቆንዳዎች ከነ ዲግሪያቸው ለከፈውኝ ተገቢውን የማቆሚያ ቀጠናቸው ይዘዋል። ልካቸው ስላወቁ አመሰግናቸዋለሁ። እናንት የካልት ጫጫታ ይዛችሁ ስለ አማራ ለምን ቆምክ፤ በማለት እኔን ለመልከፍ መሞከራችሁ የባሰውኑ ከሕዝብ ጋር ያጋጫችኋል። ስለዚህ "አደብ ግዙ!" አንድ ወዳጄ በጠም ብዙ አማት ሆኖታል "እነዚህ ሰዎች አላወቅሃቸውም፤ ስትከላከልላቸው ባንዳች ምክንያት ከተቸሃቸው የኋላ ኋላ ወዳንተው ሊዞሩብህ ነው እና ባትጠጋቸው እመርጣለሁ፡ እነዚህ ሕሊናቸው የተበላሹ መያዣ የሌላቸው ዕብዶች ናቸው" ብሎኝ ነበር።አሁን ገባኝ!

ዓይጋፎረም የተባለ የወያኔ ድረገጽ ወያኔን የሚቃወም ጽሑፌን ያለ ምንም "ሴንሰር" እና የቃላት ድለዛ እንዳለ ስላወጣልኝ (ትግርኛውንም አማርኛውንም) ትችቴን በማተሙ የሚገባው ምስጋና ሰጥቼዋለሁ። እንደ አሲምባ የመሰለው ደደብ ቡድንተኛ ግን ዋለልኝን ወይንም ኢሕአፓ ያስተላለፋቸው ፕሮፓጋንዳዎች በድረገጻችሁ ሲተላለፍ ሌላው ወገን መልስ ጽፎ ወደ እናንተው ሲልክ "በራስ መተማመን እና ቡድንተኞች" ስለሆናችሁ ወደ እናንተ የሚላኩ ነገሮች አታትሙም። እኔን ያደረጋችሁኝ ያንን ነው ለሞረሽ ወገኔ ያደረጋችሁትም ያው ነው።እንንተ እና መሰል ቡድንተኞች ተቃዋሚ ነን እያለችሁ ትችታችንን ከወገንተኛነት ነጻ በሆነ አገልግሎት ሳትሰጡ የወያኔ ድረገጾች "ልብ እና ጊዜ ለውጦአቸው መሪዎቻቸው እና ድርጅታቸውን የሚተች ትችት በመለጠፋቸው ዓይጋን በማመስገኔ ትክክል ነው። እናንተ ማፈሪያዎች የኔንስ ተውት፤ ይህንን እስቲ ላስታውሳችሁ?

[በዐማሮች ላይ በሚፈፀመው አሰቃቂና ዘግናኝ ዕልቂት ላይ መሣለቅ በታሪክና በሕዝብ ያስጠይቃል በፍኖተ-ዴሞክራሲ ሬዲዮ ለቀረበው ውንጀላ የተሰጠ አጸፋዊ መልስ”]{style="color:red"} (**ማክሰኞ መስከረም ፬ ቀን ፪ሺህ፰ ዓ.ም. ቅፅ ፬ ፣ ቁጥር ፩ ሞረሽ ወገኔ** )

ሞረሽ ወገኔ የአማራ ድርጅት ምን ብሎ ነበር ስለ ወገንተኞቹ ስለ ጸረ አማራዎቹ አሲምባዎች መልስ የጻፈው። ልጥቀስ፡

<< ሠሞኑን የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ንብረት የሆነው «ፍኖተ-ዴሞክራሲ» በመባል የሚታወቀው የሳተላይት ሬዲዮ ጣቢያ በዐማራው ነገድ ተወላጆች ላይ የጅምላ ክስ አቅርቧል። ክሱ **«በአማራ ሕዝብ ስም ሌሎችን መዝለፍ የሚወገዝ ነው»** በሚል ርዕስ ያዘጋጀውን መግለጫ ነሐሴ ፳፪ ቀን ፪ሺህ፯ ዓ.ም. በሬዲዮ አስተላልፏል[1]፤ በጽሑፍ ደግሞ በተባባሪ ድረ-ገፆች «አሲምባ[2]» እና «ደብተራው[3]» አሠራጭቷል። ከሁሉም የሚያሣዝነው የ«አሲምባ» ድረ-ገፅ አስቀድሞ ለጥፎት የነበረውን የሞረሽ-ወገኔን መግለጫ ሲያነሣ እና የ«ፍኖተ-ዴሞክራሲን» መግለጫ ሲለጥፍ ለአንባብያን ሚዛናዊ አስተያየት ሲባል እንኳን ሁለቱንም መግለጫዎች ጎን-ለጎን ያለማቅረቡ ነው። ይህም የድረ-ገፁ አስተዳዳሪዎች የወሰዱትን ሚዛናዊ ያልሆነ ውሣኔ በግልፅ ያመለክታል። የ«ፍኖተ-ዴሞክራሲ» መግለጫ ዓላማ ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት **«በቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል፣መተከል ዞን በሚኖሩ ዐማሮች ላይ የተፈፀመ የዘር ማጥፋት ወንጀል»** በሚል ርዕስ ማክሰኞ ነሐሴ ፲፪ ቀን ፪ሺህ፯ ዓ.ም. የሰጠውን በሃቅና በተጨባጭ መረጃ የተደገፈውን ዘገባ ለማጣጣል ነው። ሆኖም «የፍኖተ-ዴሞክራሲ» ሬዲዮ ዝግጅት ክፍል ምንም ዓይነት የማጣራት ሙከራ ሣያደርግ፣ መግለጫ ያወጣውን ሞረሽ-ወገኔን «እንዴት ነው? ምን መረጃ

አላችሁ? መረጃው የቱን ያህል አስተማማኝ ነው? ሌላስ ሁለተኛ እና ሦሥተኛ አካል መረጃውን እንዴት ማግኘት ይችላል?» ብሎ ሣይጠይቅ **«በጉምዝ ሕዝብ ላይ የተከፈተው ጸያፍ ዘመቻ የአማራን ሕዝብ ተገን አድርጎ በመሆኑ ሊወገዝ የሚገባው ነው።»** በማለት በጭፍኑ ተበዳዩን ዐማራ መልሶ ወንጅሏል። «በደለኛ፣ በደለኛ ወታደር በደለኛ ነው፤ ነገር ግን ባላገር (ገበሬ) ይከሣል» ሆነና ነገሩ፣ «ፍኖተ-ዴሞክራሲ» በዳዮቹን የትግሬ-ወያኔ ሎሌ የሆኑትን የጉምዝ ልሂቃን ድርጊት ከማውገዝ ይልቅ በዐማራው ላይ በሚፈፀመው ዕልቂት ላይ ተሣልቋል።

ይል እና በጣም በርካታ ነጥቦችን በማንሳት ከሰነዘርዋቸው መልሶች አንዱ እንዲህ ይላል፡

**“«የጉምዝ ሕዝብ/ ቤንሻጉሎች አማራውን ገድለው ጉበቱን፣ ኩላሊቱን፣ የታፋ ሥጋውን በሉ ብሎ ዓይንን በጨው አጥቦ ሕዝብን መዝለፍ አፍሪካን ከሚጠሉ ነጮች የሚጠበቅ እንጂ፣ ለዐማራ ተቆርቋሪ ነን ባዮች ሊሰጥ የሚገባው አደለም ።»**

<< ከዚህ ላይ መግለጫውን ያወጣው የ«ፍኖተ-ዴሞክራሲ» ዝግጅት ክፍል ያሳሰበው የዐማራውን ሥጋ ጠብሰው የበሉት ገዳዮቹ ጉምዞች፣ «ለምን የሰው ሥጋ በሉ ተባሉ?» ብሎ ነው። ሥጋቸው ተጠበሶ የተበሉት ዐማሮች ለእነርሱ ምናቸውም አይደሉም፤ ሰውም አይደሉም፤ በእነርሱ ቤት ሙክት ወይም ጠቦት ናቸው። ሥቃይ የተፈጸመባቸው ዐማሮች ሳያሳዝኗቸው፣ ሥቃይ አድራሾቹ ጉምዞች እንዴት ሊያሳዝኗቸው ቻሉ? በመሠረቱ የ«ፍኖተ-ዴሞክራሲ» ዝግጅት ክፍል በሬዲዮ ያስተላለፈውን እና በጽሑፍ ያዘጋጀውን መግለጫ ሲያሰራጭ ያጣራው አንዳችም ነገር የለም። ቢያጣሩ ኖሮ እንዲህ ያለ ከሃቅ ጋር የሚጣረስ መግለጫ ባላወጡ ነበር። ልብ ካላቸው መልካን እና አይጋሊ-ሞዛምቢክ ቀበሌዎች (መተከል) ስልክ ደውለው ጉምዞችን ቢያነጋግሩ፣ ጉምዞች በባህላቸው ውሸት ነውር ነውና፣ «አዎ ዐማሮችን አርደን በላናቸው! ሥጋቸው ይጥማል፤» እንደሚሏቸው አንጠራጠርም!”

ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት ለሁለት ወገን፦ ለበዳዩም ሆነ ለተበዳዩ፣ ጥብቅና አይቆምም። የቆመው በአሁኑ ዘመን አንዳችም ተሚጋች ጠበቃ ለሌለው ለዐማራው ነው። በዐማራው ላይ የደረሱ ችግሮችን፣ ከነችግሩ ምንጮች እና ችግር አድራሾቹ በመረጃ በማስደገፍ የተለያዩ መግለጫዎችን አውጥቷል፣ ለወደፊቱም ያወጣል። ሥራችን ወንጀለኞችን ማጋለጥ እና ለፍርድ ማቅረብ ስለሆነ ወደፊትም ይህ አሠራራችን ይቀጥላል። እንደ ሞረሽ-ወገኔ እምነት በዐማራው ላይ በማንኛውም ዘመን ወንጀል የፈጸሙ የማናቸውም ነገዶች ልሂቃን እና ተወላጆች እንዲሁም የፖለቲካም ሆነ «የእገሌ ሕዝብ ነፃ አውጪ ነን» ባይ ድርጅቶች በሕግ መጠየቅ አለባቸው ብለን እናምናለን። ጉምዞችም በትግሬ-ወያኔዎች ጃዝ-ባይነት ወገኖቻችንን ዐማሮችን አርደው በልተዋቸዋልና እንፋረዳቸዋለን። የዚያን ጊዜ የ«ፍኖተ-ዴምክራሲ» ዝግጅት ክፍል እና በባለቤትነት የያዘው ድርጅት ኢሕአፓ ጥብቅና መቆም ይችላል።>>

**<< 5 «ሕዝባችን ሰው አይበላም፤ ይህን ውሸት ማሰራጨት ኢትዮጵያ ላይ መዝመት ነው።»**

<< በመጀመሪያ ደረጃ ሞረሽ-ወገኔ ያሠራጨው መረጃ ሐሰት መሆኑን በተጨባጭ መረጃ ተመርኩዞ ለአንባቢ እና አድማጭ ሳያረጋግጡ «ውሸት ነው» ማለት ተገቢ አይደለም። ለመሆኑ የ«ፍኖተ-ዴሞክራሲ» ዝግጅት ክፍል በመሬት ያለውን ሃቅ ለማጣራት ምን ሙከራ አድርገዋል? ወይስ ሰው-አልባ የስለላ አውሮፕላን (drone) ወደሥፍራው ልከው አረጋግጠዋል? ካቀረቡልን ሐተታ ግን ይህንን ሃቅ ሊያስተባብሉበት የሚችሉበት አንድም መረጃ የለም። አልያ ሃቁን ለማስተባበል ወያኔያዊ ሥራ መሥራት

ይኖርባቸዋል። ስለሆነም ድርጊቱ የተፈጸመ ስለሆነ ሞረሽ-ወገኔ ትላንትም ሆነ ዛሬ ያለው አቋም አንድ ነው፡- በመተከል ዞን መልካን እና አይጋሊ-ሞዛምቢክ ቀበሌዎች ጉምዞች ዐማሮችን ገድለው ሥጋቸውን በልተውታል። ደረቁ ሃቅ ይህ ነው!>>

7 **« የጉምዝ ቤንሻንጉልን ሕዝብ በጸያፍ ውንጀላ የከሰሱ ሁሉ ሕዝብን ይቅርታ መጠየቅ አለባቸው፤»**

<< ልብ በሉ ወገኖች፣ የ«ፍኖተ-ዴሞክራሲ» ሬዲዮ ዝግጅት ክፍል በአሠቃቂ እና አረመኔያዊ ሁኔታ ለተገደሉት እና ሥጋቸውን ለተበሉት፣ እንዲሁም ኃብት ንብረታቸውን ተቀምተው ለተፈናቀሉት ዐማሮች አላዘነም። ይባስ ብሎ ጥብቅና የቆመው ለወያኔ እጅታ ሆነው ዐማራውን ለገደሉት እና ሥጋውን ለበሉት የጉምዝ ሰዎች ሆነ። አልፎ ተርፎም «እንዴት ጉምዞች እንዲህ ይባላሉ?» ብሎ እኛን ሞረሽ-ወገኔን ይቅርታ እንድንጠይቅ ያስጠነቅቃል። ይቅርታ የሚጠይቅ እኮ ጥፋት ያጠፋ፣ የዋሸ፣ የሰረቀ፣ የገደለ እንጂ እውነቱን የተናገረ አይደለም። ስለዚህ ሞረሽ-ወገኔ የዐማራ ድርጅት ባወጣው መግለጫ አጥፊዎቹን የጉምዝ ነገድ ተወላጆች ይቅርታ አይጠይቅም፤ ይፋረዳቸዋል እንጂ!>> ሲል ሞረሽ አጸፋውን መልሷል።

ይህ ነው ኢሕአፓ ካልቶች ማንነት እስከዚህ ድረስ ይሄዳል። "አለና፤አለና" እያሉ በተደላደለ አገር እየኖሩ ለእንዲህ ያለ ያፈጠጠ ያገጠጠ ጸረ አማራነት ቆመው ነው "አለን" በሉን እያሉ ማፈሪያ ንትርክ ውስጥ እያስገቡን እና ድርጅታቸውንም ይባስ እንዲጠላ እያደረጉት የሚገኙ። እነዚህ ከነ ነብሳቸው የተበሉት ምስኪን ገበሬ አማራዎች አልተበሉም ውሸት ነው እያላችሁ የሞቱባቸው ዘመዶችን ጉሙዞችን ይቅርታ ይጠይቁ ስትሉ ያላፈራችሁ እኔኑን ግለሰብ "ጌታቸው ረዳ ከአማራ በላይ አማራ መሆን

ይፈልጋል ” ስትሉ ለእኔ ከነዚያ ከሞቱት ምስኪኖች በላይ በሬድዮናችሁ ስትዘልፏቸው እና ይህ ማፈሪያ ዘለፋችሁ ወደ ኢትዮጵያ ስታስተላልፉ ስለኔ ያላችሁት እሚገት ነው። አማራዎች በመንደራቸው የሚያስጠጉዋቸሁም አይመስለኝም። ይቅርታ መጠየቅ ያለባችሁ እናንተ ናችሁ።

## ዋለልኝ

1) ስለ ዋለልኝ ጸረ አማራነት እና ጸረ ኢትዮጵያዊነት እና ስለ መገንጠል ሰባኪነት እንመለከታለን፤
2) ስለ ኢሕአፓ ጸረ አማራነት እና ጸረ ኢትዮጵያዊነት እና ስለ መገንጠል ሰባኪነት አንድም ሁለትም እንመለከታለን፤

(ብዙዎቹ በሁለተኛ ቀጣይ ጹሑፌ ይቀርባሉ)

ዋለልኝ እና ኢሕአፓ አንድም ሁለትም ናቸው። እምነታቸውን እናያለን። ስለሆነም ነው፤ የአሲምባ ድረገጽ ኢሕአፓዎች ዋለልኝን የሚተች ሲያዩ በቆረቆዘው ጋንጋዊ ባሕሪያቸው ተሰባስበው እንደ አይጥ “ጺጥ! ጺጥ!” እያሉ የሚጮኹት።

ነብሳቸው ይማር እና ሟቹ ፕሮፌሰር ዓለሜ እሸቴ ኢሕአፓ፤ወያኔን እና ኦነግ ሲያጋልጡ From Baron Prochazka to Benito Mussolini "Legge Organica" the "Charter" for the Tribal Dismemberment of Ethiopia” እና ስለ ኢሕአፓ በጣና በለስ ግድብ ጣሊያኖችን ጠልፈው ስለመውሰዳቸው እና ስለ ኢሕአፓ እና ሳላሕ ሳበ እንዲሁም ስለ ኤርትራ ጉዳይ እና ኢሕአፓዎች፤ ወዘተ..... የሚሉ ጽሑፋቸው ለሕዝብ ይፋ ሲሆኑ ኢሕአፓዎች/ ወያኔዎች/ኦነጎችና ወዘተ.... ዘረኞች ምን ያህል ራዕድ/ፍርሃት ድንጋጤ እንዳደረባቸው ጽሑፉን ያነበባችሁ ዜጎች የምታስታውሱት ይመስለኛል።

ሌላው በዓይን ብርሃን መታወክ ምክንያት ከሕዝባዊ መድረክ ድንገት የተሰወረው እውቁ ምሁር የትግራይ ተወላጅ (ዓጋመ አውራጃ) ካናዳ ውስጥ የሚኖር ፕሮፌሰር ሐጎስ ገ/እየሱስ ኢትዮጵያውያን ረስተውት ስንገነዘብ እኔ እና ዶ/ር አለሜ እሸቴ Where's the great Hagos Gebreyesus? Message May 8, 2007 (ጉጉል ብታደርጉት ሙሉውን ማንበብ ትችላላችሁ) በማለት ዶ/ር ሐጎስ በሕይወት መኖሩን አወቅን። ደ/ር ሐጎስ የሚታወቀው በብዙ ትግሎችና ጽሑፎቹ ቢሆንም ከነሱ ውስጥ The Two Headed Hydra, National Self Hatred and Nihilism ..." የሚለው ኢሕአፓ፤ መኢሶን ወያኔና ሻዕቢያ ያወገዘበት የብሔር ብሐረሰብ ጉዳይ ነበር። ሓጎስ በተጨማሪ

1) The New Infantilism: Problems and Prospects of the. Ethiopian Student Movement, unpublished paper, presented at a meeting in. Halifax, Canada, July 1972 (*Hagos* Gebre Yesus (1972).

2) The Bankruptcy of the Ethiopian 'Left': Meison-EPRP, A. *Two-Headed Hydra* – (*Hagos* Gebre Yesus (1977)

በሚል የጻፋቸውን የተመለከተ አንባቢ የተበላሸ የኢሕአፓ እና ጸረ አማራ የነበረው ግራ ዘመም የ60ዎቹ የተማሪው አስተሳሰብ በደምብ ይገልጻል። ሓጎስ በዛው ዓለም አላለፈም ሳይሆን፤ የታዘበው ግን ለኛ ከውስጡ የታዘበው እኛ እውስጥ ላልነበርነው እና መጪው ትውልድ አንባቢዎች በሚገባ ታሪኩን ሰነዱን እንድንመለከተው አድርጓል።

ኢሕአፓዎች እና መኢሶኖች "ያንድ ዘንዶ ሁለት ራስ" ይላቸዋል። እኔ እና ፕሮፌሰር አለሜ እሸቴ ሓጎስን አፈላልገን አግኝተን ጹሑፎቹን

ስናሰራጭ ኢሕፓዎች “እንደ ዓይጥ “ጺጥ-ጺጥ” ማለት ጀመሩ። እኔ እና ፕሮፌሰር ስቀን አላቆምንም።

ዋለልኝ መኮነን

ዋለልኝ ጓደኛው ነበርኩ የሚል አንድ ቅዠታም የወሎ ሰው አለ “ሲያትል ውስጥ የሚኖር” (ትግራይን ዳግማዊት ጉዲት መጥታ አፈር ድቤ የምታበላችሁ እንልካለን) እያለ የሚቃዥ ጸረ ትግሬ ሰው አለ እኔን “ወያኔ ነው” እያለ አረፋውን ደፍቆ ደክሞት ዛሬ አሲምባ ላይ “በስተ እርጅናው” አለፍ ብሎ ሲሞነጫጭር አየዋለሁ። ግን እሱም ቢሆን እግዚሃር ይስጠው በዚህ አመሰግነዋለሁ “ዋለልኝ ለምን ተነካ” ብሎ እንደ  ወያኔዎች እና ኢሕአፓዎች  ጨርቁን ጥሎ አያብድም።

ኢሕአፓዎች ዋለልኝን አትንኩ የሚሉለት ዋለልኝ መኮንን ማነው ነው?

ከ11 አመት በፊት ፕሮፌሰር አለሜ ከጣሊያን አገር ጽፈው አሰራጨው ብለውኝ ድረገጾች ላይ የተለጠፈው በብዛት ያሰራጨሁት “**ON THE QUESTION OF ETHIOPIAN NATIONLITIES” WALELEGN AS ROMAN PROCHAZKA**

የሚል ጽሑፍ ዋለልኝ መኮንን **ON THE QUESTION OF ETHIOPIAN NATIONLITIES”** የሚለው ጽሑፉ በየድረገጹ ያሰራጨናቸው ይህ ሰነድ ነበር። ፕሮፌሰር የዋለልኝ ጽሑፍ “The Hot Bed of Anti Ethiopia” ይሉታል። “ጸረ ኢትዮጵያ ሃይሎች የሚተኙበት የተመቻቸው የሞቀ የመኝታ አልጋቸው” ይሉታል።

አዲስ አበባ ባንድ አምባሲ የሕግ አማካሪ የነበረ ፕሮቻዝካ የተባለው አውስትርያው የናዚ አምላኪ  “አቢሲኒያ የባሩድ በርሜል” (Abyssinia the powder Barrel) ብሎ ኢትዮጵያ የምትባል አገር ካሁኑኑ ካልበታተንናት ለነጭ የማትገዛ ሃይለኛ ከሚባሉት አገሮች ሆነ እንደምትወጣ እርግጠኛ ስለሆንኩ አማራና ክርስትያን የሚባሉ ጨቋኝ ክርስትያን ያልሆኑትን ሌሎቹን ነገዶች አማራ ከሚባል ጨቋኝ ነፃ

ለመውጣት ስለሚፈልጉ ፍላጎታቸውን ለማሳካት እና አገሪቷን እንድትበታተን ካላደረግን የጥቁር ሕዝቦች አሸናፊነት አርማ መሆኗን ስለማይቀር “ከጃፓን ጋር ግምባር ፈጥራ ጸረ ነጭ ሃይል ሆና” የምዕራቡን አገር ባህል እና ስልጣኔ ከመቀናቀንዋ በፊት አማራውን ማስጠላት እና ሌሎችን ጸረ አማራ እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ አለብን፡ ብሎ መጽሐፍ ጽፎ ለዓለም ሕዝብ ያሳወቀ ናዚ ነው።

ያንን ምክር በመቀበል ዋለልኝ የቀሰመው እና የባሰውን አሻሽሎ **ON THE QUESTION OF ETHIOPIAN NATIONLITIES” By Walleligne Mekonnen November.17,** 1969) በፈረንጅ አቆጣጠር ስለጻፈ ነው ፕሮፌሰር አለሜ እሸቴ ON **THE QUESTION OF ETHIOPIAN NATIONLITIES” WALELEGN AS ROMAN PROCHAZKA** ሲሉ ሊጽፉበት የቻሉት።

እስኪ ኢሕአፓዎች እንደ መልአክ የሚያመልኩት እና ተነካ ብለው የሚንጫጩብን ዋለልኛቸው ጸረ አማራ እና ጸረ ኢትዮጵያዊነቱን እንደገና ሳይሰለቸን ጥቂቶቹን ነጥቦች አንስቼ ቢቀጥለው ክፍል አቻምየለህ ስለ ኢሕአፓ ያጋለጠው ሰነድ  እና እኔ የምተቸው ስለ ዋለልኝ ሰነዶች ስለምቀርብ ለመደምደሚያ ግን ይህንን ነጥብ ጠቅሼ ልደምድም፡

ዋለልኝ የሚለን፡
ኢትዮጵያ አንድ አገር አይደለችም ይላል።
“What are the Ethiopian peoples composed of? I stress on the word peoples because sociologically speaking at this stage Ethiopia is not really one nation. It is made up of a dozen nationalities with their own languages, ways of dressing, history, social organization and territorial entity. And what else is a nation? It is not made of a people with

a particular tongue, particular ways of dressing, particular history, particular social and economic organization? Then may I conclude that in Ethiopia there is the Oromo Nation, the Tigrai Nation, the Amhara Nation, the Gurage Nation, the Sidama Nation, the Wellamo [Wolayta] Nation, the Adere [Harari] Nation, and however much you may not like it the Somali Nation.This is the true picture of Ethiopia.”

ይህ የዘመኑ ቅራቅምቦ የታመሪው እውቀት እና የአገር ትንታኔ ካሁን በፊት መልስ ሰጥቼበታለሁ። በዋለልኝ የዘመኑ ትንሽየ መነጽር “አንድ አገር” ተብሎ እንደ “አገር” ለመጠራት አንድ ቋንቋ፤ አለባበስ፤ አመጋገብ፤ አስተሳሰብ፤ ታሪክ..የያዘ ሲሆን እንጂ እንደ ኢትዮጵያ የመሰለ የተለያዩ ቋንቋዎች፤አለባበሶች ታሪኮች፤ባህሎች ምግቦች ያላት አገር ለማለት አያስችልም” ይላል። ይህ በጣም የሚያስቅ ነው። እንዲህ ያለ አገር አለ ተብሎ የማይታሰብ እኮ ነው በሕልም እያወራ ያለው። የምን ሶሲዮሎጂ እየወራ እንደሆነ ለኔ አልገባኝም። እንኳን የ20 ሚሊዮን ሕዝብ አገር ይቅር እና ባንድ ቤተሰብም የትም ዓለም የተለያዩ ልብሶች፤ የተለያዩ ምግቦች ፍላጎት፤ አስተሳሰቦች፤ ሃይማኖቶች ይከተላሉ። ስለዚህ አንድ ቋንቋ፤ልብስ፤ምግብ አረማመድ፤ሃይማኖት የግድ መኖር የለባቸውም (አገር ለመባል)። ሳውዲ አረቢያ እንኳ የተለያዩ “ነገዶች እና ሃይማኖቶች፤ መደቦች፤ አስተሳሰቦች አሉዋቸው። የፕሮቻዝካ ጽሑፍ ስታነቡ ልክ ዋለልኝ የሚያወራው ነው ቀድቶ ገልብጦ ያቀረበልን።

የነ “ፋኖን” መጽሐፍ በማንበብ በስሜት የተወነጨፈው ወጣቱ ዋለልኝ “አገር ማለት አንድ የቋንቋ ልሳን፤ አመጋገብ፤አለባበስ፤ አንድ የተሳሰረ ማሕበራዊ፤ምጣኔ ሀብታዊ፤ እና ተመሳሳይ የጋራ ታሪክና ድምበር፤ ሲኖረው ብቻ ነው አገር/ብሔር ወይንም አንድ ሕዝብ ሊባል የሚቻለው፡ ካልሆነ ግን ኢትዮጵያ የብሔሮች ስብስብ እንጂ፤ ይህንን ያላሟላች ባሁኑ

ጊዜ እራስዋ የቻለች አንድ ወጥ የሆነች አገር አይደለችም"። ይላል። ብሔር በትክክለኛ ትርጉሙ "አገር ማለት ነው"። ዋለልኝ የሚለን ደግሞ ኢትዮጵያ የተለያዩ አገሮች ያቀፈች ብሔር/አገር ነች ይለናል። አገሮች የሚላቸው ደግሞ ሲተነትን ኦሮሞ ነሺን/ ብሔር/አገር አማራ ነሺን/አገር/ብሔር ሲዳማ ጉራጌ ነሽን/ አገር ወዘተ…ወዘተ. የተባሉ አገሮች በኢትዮጵያ ውስጥ አሉ። ይላል።

የፋኖን መጽሐፍ አንባቢው ዋለልኝ ሊቃጣው የፈለገው "ኢትዮጵያ የተጠቀሱትን አገሮች/ብሔሮች ኮሎኒያሊስት ነች" ለማለት ነው።

እንደ አገር ሳይሆን አንደ ጭቃ ተጠፍጥፋ አማራዎች እና ትግሬዎች

ያገጣጠሟት አሁንም የሚገዝዋት "የውሸት ስራ የሆነች አገር በመባል የምትጠራ "ፌክ ኢትዮጵያ" የምትባል በአማራ ገዢዎች የሚቀሰቀስ ኢትየጵያዊ ስሜት እንጂ በውስጧ የሚኖሩ ኗሪዎቻ ኢትዮጵያዊ ብሔራዊ ስሜት የሌላቸው የውሸት አገር ነች" ሲል ይወነጅላል። ዓድዋ፤ ማይጨውና የመሳሰሉ ኢትዮጵያዊነት ስሜትን ለዓለም ያስመሰከረ ሕዝብ "በውሸት ስሜት" የሚነዳ ሲል ሕዝብን ይዘልፋል። ስለ አገሪቱ ብሔራዊ ስሜት የመሰከሩ የውጭ የታሪክ ሰዎችም አብሮ ይገርፋቸዋል።

PREVAIL – THE WAR IN AFRICA THAT CHANGED THE WORLD [Book Trailer]

https://youtu.be/iN3wCyfDbwY

በምንሊክም፤ በሃይለስላሴም ዘመን ጠላት አገሪቷን ለመውረር ሲመጣ፤ ኦሮሞ፤ አማራ፤ትግሬ፤ጉራጌ፤እስላም ክርስትያን ሰይል ባብዛኛው ፤በብሔራዊ (ሃጋራዊ) ስሜት ተነስቶ ጠላት ድል በመምታት፤ ሊደርስ የነበረው ውርደት ቀንሶ አንዳንዴም ጭራሸኑ

ዓለም በሚያስገርም ጀብዱ ተዋግቶ ጠላትን አሳፍሮ መልሶዋቸዋል። እነኚህ ልባቸው፤ቀ፤ቀባቸው፤ ሕሊናቸው አካላቶቻቸው ሁሉ ባገር ፍቅር፤በብሔራዊ ስሜት የተገነባ ነው።

ያውም በተደጋጋሚ! እነ ዋልልኝ "ፌክ'ኢትዮጵያ፤ "ስሜት ቢስ ዜጎች፤ እያለ ያዋረደው ሕዝብና አገር።ዋልልኝ ያ ሁሉ ጀግንነትና ጀብዱ፤የገዢ መደቦች ብሔራዊ ስሜት ያነሳሳው፤የገነባው እንጂ ሐቀኛ ሃገራዊ ስሜት የተንጸባረቀባት አገር አይደለችም፡ ይላል። ከላይ የሰጠኋችሁ የመጽሐፍ/ቪዲዮ ማስታወቂያ፤ ጣሊያን ሲወጋን፤ ብሔራዊ ስሜታችንን ለመግደል ሲዘምትብን፤ እንኳን ኢትዮጵያዊያን ቀርቶ፤ የውጭ ዜጎችም (ዋለልኝ ተጓዦች/ጎብኚዎች ይላቸዋል ሲያሳንሳቸው) ብሔራዊ ስሜታቸው ከኢትዮጵያዊያን ጋር አብሮ ስለነጎደ ፤ስሜታቸው ተጋግሎ በመላው ዓለም ያደረጉት ሰላማዊ ሰልፍ በቪዲዮው እዩት። የዋለልኝ ስሕተት በግልጽ ይታያችኋል።

አገራዊ ስሜት ሽማግሌዎቹ ብቻ ሳይሆኑ ወራሪ ሲመጣ ወጣቱም በእንዲህ ያለ አገራዊ ስሜት ተገንብቶ ነበር ጠላትን ያርበደበደው፤



ከእነዚህ ከላይ በፎቶግራፍ ከተመለከትናቸው የአገር አርበኞች የተላላፈ ብሔራዊ ስሜት፤ የትግራይ ፋሺስት ግልገሎቹ ከትግራይ ገስግሰው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ላይ ሰላማዊ ሰልፈኞች ላይ የወደብ ጉዳይ እና የኤርትራ ግንጣላ የሴራና የባንዳዎች ውሳኔ ነው ብለው የግራዘያኒ ጥይት እሩምታ ሲያወርዱባቸው፤ የኢትዮጵያ ፈጣሪ ይመስገን "ኢትያዊ ብሔራዊ ስሜት" አልጠፋም ነበር። ይህንን ታሪካዊ እና rare/ የማይገኝ እግዚሄር እራሱ ያነሳው ታአምራታዊ የአምላክ ስራ/ፎቶን" አብርን እንመልከት። አሌፍ በተባለው መጽሔት ታትሞ ነበር። እነሆ። ዋለልኝን አትንኩ የምትሉ ማፈሪያዎች ማፈር አለባችሁ።




ዋለልኝ፤ "There is of course the fake Ethiopian Nationalism advanced by the ruling class and unwillingly accepted and even propagated by innocent fellow travellers. ይላል።

ዋለልኝ በህይወቱ እያለ የሕዝቡ ኢትዮጵያዊ ስሜት እንዴት ግሎ እንደነበርና “በአገርና በሚስት የለም ዋዛ” ብሎ መመሪያው ያደረገ “አንድ” ሕዝብ፤ እንዴት እንዳልገባው ባይገባኝም፤ በሃገራችን የታዩ ተደጋጋሚ ጀብዶች (ከጦርነት እስከ ስፖርት) የገዢ መደቦች የፈጠሩት ከሆነ፤ ከሕዝቡ ይልቅ ለገዢዎች ግርማ ሞገስ መስጠቱ የዋለልኝ ግምገማ ለእኔ አስገርሞኛል።

ገዢዎች መመስገን የሚገባቸው ቦታና ክብር ፣መስጠት ያለ ነው፤ ምክንያቱም ሃገራዊ ስሜቶች መሪዎች ናቸው የሚመሩት፤ከዚያም ሕዝቡ ሆ ብሎ ይከተላል።ሆኖም የተገኙት ድሎች ያለ ብሔራዊ ስሜት የተገኘ ነው ብሎ የሚያምን ምሁር ሁሉ “ያስተሳሰብ ችግር አለበት ማለት ነው። የዓለምን ኢምፔሪያሊስት ወራሪ ፋሺስት ዓድዋ ተራሮች ላይ “ማማ ሚያ!!!!እማዬ ሆይ! እማዬ ድረሺ!” እስኪል፤ በእምብርክኩ ያስኬደው ኢትዮጵያዊ ብሔራዊ ስሜት የት ሊደበቅ ነው? የሕዝቡ ኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜት ያመነጨው ድል ካልሆነ ምን ተብሎ ሊጣራ ነው?

የመጠቁ የተመነደጉ ተማሪዎችና አንዳንድ የወቅቱና የዛሬ ምሁራን አማራ ስለሚጠሉ፤ አማራን በገዢ መደብ ስለሚመድቧቸው፤ መሪዎችን እየዘለፉና ያሳነሱ እየመሰላቸው የሕዝቡን የጀብዱ ተሳትፎ፤ ከሕዝቡ ነጥቀው “የአማራ ነው” የገዢ መደብ ነው” እያሉ እራሳቸውን ያስገምታሉ። ጥላቻ እስከዚህ ድረስ የሕሊናን ሚዛን ይጋርዳል።

ክፍል ሁለት ይቀጥላል፡

ጌታቸው ረዳ (ኢትዮ ሰማይ ድረገጽ አዘጋጅ)

getachre@aol.com